Washington State Department of Social & Health Services
Transforming lives

# ICAP / SIB-R የመልመድ ባህሪ ለመሙላት መመርያ
## Guidelines for Completing the ICAP / SIB-R Adaptive Behavior Scale

የ ICAP የመልመድ ባህሪ ክፍል የአመልካችን የዕለታዊ የኑሮ ክህሎትና አመልካቹ እነዚህን መቼ ማድረግ እንዳለበት ማወቁን ይመግማል፡፡ የዚህ ዓላማ ያለውን/ያላትን አቅም ለማወቅ ነው፡፡ አንድን ስራ ለመስራት ሳይጠየቅ ወይ በተደጋጋሚ ሳይታወስ ለመስራት የማገናዘብ አቅም ወይ እውቅና ከሌላት/ከሌለው ነገሮችን የመልመድ ባህሪ ውጤት ዝቅ ሊል ይችላል፡፡

**ስራውን ያለ ድጋፍ ወይ ክትትል ሙሉ በሙሉ ይሰራል (ወይ መስራት ይችላል)**

*ስራውን ሙሉ በሙሉ ይሰራል ማለት ሁሉንም ክፍል ማለት ነው፡፡* አንዳንድ የICAP የመልመድ ባህሪዎች ከአንድ ክፍል በላይ አላቸው፡፡ አንድ ሰው በአንድ የስራ ክፍል ጥሩ ከሰራ በአንድ ክፍል ደግሞ መሃከለኛ ከሰራ ውጤት ሲሰጡ ጥሩ ተሰርቷል ብለው ውጤት ይስጡት፡፡

*መስራት ይችላል፡፡* አንዳንድ ጊዜ አመልካቹ በደምብ የሚችለው ወይ በከፊል የሚችለው ስራ ይኖራል ነገር ግን የመስራት ዕድል ላያገኝ ይችላል፡፡ ምናልባት ይህ እንቅስቃሴ ከሌለ፣ ከሕግ ውጪ ከሆነ ወይ ‹‹የሌላ ሰው ስራ›› ከሆነ፡፡ በዚህ ሁኔታ ይህ ሰው ዕድሉ ከተሰጠው ስራውን አሁን፣ ያለ ተጨማሪ ስልጠና፣ ድጋፍ ወይ ክትትል ምን ያህል መስራት ይችላል ብለው ይገምታሉ፡፡

*ያለ ድጋፍ ወይ ክትትል፡፡* ይህም ማለት አመልካቹ ስራውን ራሱን ችሎ መስራት ይችላል ማለት ነው፡፡ አልፎአልፎ የሚሰጥ ማበረታቻ ወይ ማስታወሻ ተቀባይነት አለው፡፡ ነገር ግን ተደጋጋሚ ጥያቄ፣ ወይ ማበረታቻ ወይ ማስታወሻ እንደ ድጋፍ ወይ ክትትል ይቆጠራሉ፡፡

በእያንዳንዱ ICAP የመልመድ ባህሪ ምድብ ውስጥ ስራዎቹ ከመሃከለኛ እስከ ከባድ እንዲሁም ከህፃንነት አዋቂነት ደረጃ ይዘረዝራሉ፡፡ እያንዳንዱ ስራ አመልካቹ ድጋፍ ወይ ክትትል ሳይደረግለት የመስራት አቅሙን መሰረት በማድረግ እያንዳንዱ ውጤት ስኬል ከ0 እስከ 3 ተዘርዝሯል፡፡

**በጣም ጥሩ ይሰራል፡፡** ይህ በስራው ላይ ሙሉ በሙሉ ራሱን ችሎ እንደሚሰራ ያመላክታል፡፡ አመልካቹ ይህ ስራ አይሰራውም ወይ ቀላል ስለሆነ አይተገብረውም (ለምሳሌ አብዛኛው ጊዜ ከማንኪያ ይልክ በሹካ ይበላል፡ አብዛኛው ጊዜ አይደህም ይራመዳል)፡፡ አመልካቹ ያለምንም ድጋፍ ወይ ክትትል አጠቃላይ የስራውን ከፊል ይተገብራል፡፡

**ሁሉ ግዜ ወይ ሁሉ ግዜ ማለት ይቻላል- ሳይጠየቅ፡፡** *ሁሉግዜ* ማለት አስፈላጊ በሆነበት ሰዓት ማለት ነው፡፡ *ሳይጠየቅ* ማለት ደግሞ ከአንድ ግዜ በላይ ሳታስተውሰው ፡፡ አመልካቹ ክህሎቱ ሊኖረውና *እንዲሁም* መቼ መተግበር እንዳለበት ማወቅ አለበት፣ ይህም በተለመደው ማሕበራዊ መለክያ መሰረት በማድረግ፡፡ ስራውን ከመጀመሩ በፊት በተገቢ መልኩ ፈቃድ ከጠየጠቀ ችግር የለውም፡፡

**ጥሩ ይሰራል፡፡** ይህም አመልካቹ ያለምንም ድጋፍ ወይ ክትትል ሁሉንም የስራ ክፍል እንደሚሰራ ያመላክታል፡፡

**ወይ ¾ ግዜ - ብዙዎች መጠየቅ አለባቸው፡፡** ይህም ሲተረጎም ስራው ጥሩ ይሰራል ብዙ ግዜ ¾ ይሰራል ወይ ¾ ያለ ድጋፍ ወይ ክትትል ይሰራል ማለት ነው፡፡ አመልካቾች አንድን ተግባር መፈፀም እንዳለባቸው መጠየቅ ወይ ማስታወስ ካስፈለጋውም ችግር የለውም፡፡

**ይሰራል፣ ጥሩ ግን አይደለም** ይህም ማለት አመልካቹ አንዳንዴ ከሰው ድጋፍ ወይ ክትትል ሳይደረግለት ሙሉ በሙሉ ወይ በከፊል ስራውን ይሰራዋል ወይ ለመስራት ይሞክራል፣ ነገር ግን ውጤቱ ጥሩ አይደለም፡፡

**ወይ ¼ ግዜ - አብዛኛው ግዜ መጠየቅ አለበት፡፡** ይህም ማለት ስራው ይሰራል ነገር ግን በተገቢ መልኩ አይሰራም፣ ¼ ግዜ ብቻ ይሰራል ወይ ¼ ግዜ ያለ ድጋፍ ወይ ክትትል ይደረጋል ማለት ነው፡፡ አመልካቾች አንድን ተግባር መፈፀም እንዳለባቸው መጠየቅ ወይ ማስታወስ ካስፈለጋውም ችግር የለውም፡፡

**በፍፁም ወይ አልፎአልፎ፡፡** ይህም የሚያመላክተው ስራው ከባድ እንደሆነና ስራው ደህንነት ያልተጠበቀ ስለሆነ ወይ ስራውን ሙሉ በሙሉ ሰርቶ ስለማያውቅ አመልካቹ ይህን እንዲፈፅም አይፈቀድለትም፡፡

**ምንም እንኳን ቢጠየቅም፡፡** ቢጠየቅ ወይ ቢበረታታም በደንብ አይሰራም፡፡

**‹‹ጥሩ›› የሚባለው ምን ያህል ነው?**

ICAP በ1.764 ዕድሚያቸው ከህፃን እስከ ሶስት ወር ህፃናት እስከ አዋቂ አካል ጉዳተኞች ያካትታል፡፡ ወላጆች ልጃቸውን (እንዲሁም አዋቂዎች ራሳቸውን ይለካሉ) በ ICAP ለመለካት የ ICAP መለኪያ ይጠቀማሉ፡፡ ይህን ስራ በጣም ቀላልና ቀጥተኛ ሆነው አግኝተውታል፡፡ ስለ እያንዳንዱ እቃ ተጨማሪ መረጃ አልተሰጣቸውም፣ ወይ አልጠየቁም፡፡

ICAP የሚለመድ ባህሪ በዕድገት ደረጃ መሰረት ነው፡፡ ስራው ምን ያህል እንደተሰራ ለመወሰን ወላጆች ተመሳሳይ ዕድሜ ላይ ያሉትን እኩዮቻቸውንና ዕለታዊ እንቅቃሴያቸወን ግምት ውስጥ በማስገባት ውጤታቸውን ይገመግማሉ፡፡ ለምሳሌ በመቀስ *በጠባቡ ቀጥ አድርጎ በመስመር መቁረጥ* መውሰድ እንችላለን፡፡ ይህ ክህሎት ዕድሚያቸው 3 ለሆኑት ነው፡፡ **ጠባብ ስንል ምን ያህል ጠባብ ነው? ቀጥ ያለ ስንል ምን ያህል ቀጥ ያለ?** *ራሳችሁን በወላጆች ጫማ አስገቡና የፕሪስኩል እንቅስቃሴ መከታተል፡፡* ጠባብ መስመር ስንል አንድ በማርከር የተሳለ ሊሆን ይችላል፡፡ ቀጥ አድርጎ መቁረጥ ስንል በስምንት ኢንች መስመር ሊሆን ይችላል፡፡

*ቀላል፣ ወይ ንፁህ* ወይ *ተገቢ* በሚሉት ቃላት ዙርያ ከተቸገሩ እራሶን የሚከተለውን ይጠይቁ፡ አካል ጉዳት ለሌቸው ሰዎች በዚህ ስራ ላይ የሚቀመጠው የእድገት ደረጃ ምንድን ነው? በዚህ ዕድሜ ያሉትን ልጆች ስኬታማነትን ለመለካት ምን ዓይነት መለኪያ ይጠቀማሉ፡፡

ንፁህ ክፍል የምንለው ንፁህናው ምን ያህል ነው? 11 – 15 ዕድሜ ልጆች ያላቸው ወላጆች ልጆቻቸው ሀላፊነት እንዲወስዱ ይጠበቃል፡፡ በዚህ ዕድሜ ልጆች ያላቸው ወላጆች ‹‹ይሰራል፣ ነገር ግን በሚገባው አደለም›› ወይ ‹‹በደምብ ይሰራል›› ሲሉ ምን ማለታቸው ነው?

የአእምሮ ወይ አካል ጉዳት ያለባቸውን አዋቂ ሰዎች መገምገም ከባድ ሊሆን ይችላል ምክንያቱ ባህሪያቸው ከማንኛውም ሰው የተለየ ሊሆን ስለሚችል ነው፡፡ ቢሆንም የውጤታማነት መለኪያ ከማንኛውም ቡድን ጋር ተመሳሳይ መሆን አለበት፡፡

**የተለመደ፣ ያልተለመደና ያለመተባበር ባህሪ መለየት፡፡**

በአመልካቾች አፈፃፀም ጥራት መካከል ልዩነት ካለ (ለምሳሌ ሁሉግዜ ወይ ሁልግዜ ማለት ይቻላል) እንዲሁም ድግግሞሽ (ለምሳሌ ¾ ግዜ)፣ ውጤቱ በመጀመርያ የጥራት አፈፃፀም መሰረት መሆን አለበት፡፡ የ ICAP የመልመድ ባህሪ ትኩረት ማድረግ ያለበት ብቃት ላይ ነው፡፡ የደከመው፣ የተበሳጨ ወይ የተናደደ ሰው አንዳንድ ግዜ ስራ መስራት ሊቃወም ይችላል ነገር ግን *ሳይጠየቅ ጥሩ ይሰራል* የሚል ሊሰጠው ይችላል ይህም ከዚህ ቀደም ይሰራበት የነበረበትን ደረጃና አቅም በመገምገም ነው፡፡ ይህ እምቢተኝነት የማያቋርጥ ከሆነና ነገር ግን በተወሰኑ የመልመድ ክህሎቶች ላይ ብቻ ከሆነ በዚህ ስራ ከአመልካቹ የመልመድ ነጥብ አንድ ይቀንሳል፡፡ አለመተባበር እንደ ባህሪ ችግር ተደርጎ አይወሰደም፡፡

በአመልካቹ የዕለት ዕለት እንቅስቃሴ ወይ ከሱ/እሷ ዙርያ ያሉት ሰዎች በሚያደርጉት እንቅቃሴ ጣልቃ የሚገባ ባህሪ ካለ ያህሪ ችግር ተደርጎ ይወሰዳል፣ የመልመድ ባህሪ *ችግር* ተደርጎ አይወሰድም፡፡ የማድረግ ችሎታ እያለው አስፈላጊውን ስራ ለማድረግ ፈቃደኛ አለመሆን፣ አንዳንድ ግዜ ያለመተባበር ባህሪ ተብሎ በ ICAP እንደ ችግር ባህሪ ተደርጎ የሞወሰደው ይህ ተቃውሞ በተደጋጋሚ የሚከሰት ከሆነ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ አመልካች ያለመተባበር ከመልመድ ባህሪ ውጤት ጋር አይያዝም፤ ውጤት መሰጠት ያለበት ያለውን አቅም መሰረት በማድረግ እንጂ ትብብርን መሰረት አድርጎ አይደለም፡፡

**ሌላ ግምት ውስጥ የሚገቡ**

**አካላል ጉዳተኝነት**

አመልካቿ አእምሮ አቅም ቢኖራት አካል ጉዳት ስላላት ድጋፍ ካልተደረገላት መስራት የማትችል ከሆነ ስራው ‹‹በፍፁም ወይ አልፏአልፎ›› (ወይ መካከለኛ ደረጃ) በሚል መያዝ አለበት፡፡ አመልካቹ አካል ጉዳት ስላለበት መሸለም ወይ መቀጣት የለበትም፡፡ ዊልቸር የሚጠቀም ሰው፣ ለምሳሌ *ሙሉ አሰቤዛ ማንሳትና መሸከም* የሚለውን ራሱን ችሉ መስራት ይችላል የሚለው ግምገማ ክረዲት ሊያገኝ ወይ ላያገኝ ይችላል፡፡

**የተለመዱ መሳርያዎችን መጠቀም**

አመልካቿ ራሷን ችላ የተለመደውን መሳርያ መጠቀም ከቻለች ማለትም ያለ ምንም ድጋፍ ከተጠቀመች የዚህን ውጤት እንደተሰራ ይወሰዳል፡፡ መነፀር ካደረገች፣ በመነፀር ምን ያህል ታያለች? ወደ ኬን ምን ያህል መሄድ ትችላለች? ምንም እንኳን ማንኪያ ብትለምድም በማንኪያ አድርጋ ምን ያህል መብላት ትችላለች?

**መድሀኒቶች፡**

መድሀኒትም እንደ መነፀር ወይ ማዳማጫ መሳርያ የሚለመድ መሳርያ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በመድሃኒት ድጋፍ አመልካቹ ምን ያህል ይሰራል?

**አማራጭ መገናኛ ዘዴዎች**

የተለመደ የምልክት ቋንቋ (ቀላል ምልክቶች ኣይደለም) መጠቀም እንደ መናገር ይቆጠራል፡፡ ኮምኒኬሽን መፅሃፍ፣ ቦርድ፣ እንዲሁም ዓረፍተ ነገር ለመስራት ብዙ ቃላትን የያዘና ከመናገር ጋር የሚመሳሰል መሳርያ፡፡ አሁን ለምሳሌ ‹‹የት›› የሚለውን ቃል ወይ ምልክት ማመላከትና ‹‹ኮት›› የሚለውን ቃል ወይ ምልክት፤ ቀላል ጥያቄ ያመላክታል፡፡ የጃኬትን ምልክት ማመላከት ወይ የጥያቄ ምልክት ማመላከት እንደ ጥያቄ ተደርጎ አይወሰድም፡፡

**መጠየቅ**

አንዳንድ የ ICAP ስራዎች በጀማሪ ደረጃ ያሉ ስራዎች ስለሆኑ ጥያቄ ለመመለስ ብቻ የሚሰሩ ናቸው (ለምሳሌ የትውልድ ዘመን መጥቀስ)፡፡ ምንም እንኳን አመልካቹ መልስ እየመለሰ ቢሆንም ባህሪው በጣም ጥሩ ይሰራል የሚል ውጤት ይሰጠዋል፡፡

**ስራው በጣም ቀላል ነው**

አመልካቹ ይህ ስራ ቀላል ስለሆነበት አሁን የማይሰራው ሊሆን ይችላል፡፡ አመልካቹ ለመስራት በጣም ቀላል የሆነለት ስራ *በጣም ይሰራል (3)* የሚል ውጤት መሰጠት አለበት፡፡ ለምሳሌ የሆነ ሰው ልብሱን በሚገባ በንፅህና መልበስ ከቻለና እንዲሁም *ሲለብስ እጅና እግሩን መዘርጋት* ቀላል ከሆነለት 3 መሰጠት አለበት፡፡

**ከአንድ ክፍል በላይ ያላቸው ስራዎች**

የተለያየ ክፍል ያለው ስራ ከሆነና አንዱ ክፍል ካለቀና ነገር ግን ሌላኛው ክፍል በከፊል ከተሰራ *ጥሩ ተሰርቷ* የሚለውን መሰጠት አለበት፡፡ አመልካቹ ሙሉ በሙሉ መስራት የማይችለው ክፍል ካለ ስራው *በፍፁም ወይ አልፎአልፎ* የሚለው መሰጠት አለበት፡፡

**ዕድል የለም**

አመልካቹ ይህን ለመተግበር ዕድል ከሌለው ወይ ከክህሎቱ ውጪ በሌላ ምክንያት እንዲሞክር የማይፈቀድለት ከሆነ፤ ለምሳሌ እንቅስቃሴው ከቤት ውስጥ ሕጊ ውጪ ከሆነ፣ ወይ ስራው ‹‹የሌላ ሰው ስራ›› ከሆነ ይህ ሰው በአሁኑ ሰዓት እድሉ ቢሰጠው ምንያህል የመጨረስ አቅም አለው የሚለውን ገምቱ፡፡

**ማፋጠን ወይ ማሳየት**

አመልካች እንዳይሰራ የተጠየቀበት ICAP ስራ ሊኖር ይችላል፡፡ ስራ ማሳየት እንዲያደርግ የሚሹት ነግ ምን እንደሆነ ለማስረዳት አንዴ ማሳየት እንደ ስልጠና ወይ ክትትል ተደርጎ አይወሰድም፡፡

**ደህንነት ጥበቃ**

አመልካቹ ባለው የስራ አፈፃፀም ደረጃና/ወይ ለሂወቱ አደጋ ይሆናል ተብሎ ስለታሰበ ምክንያት ስራውን እንዳይሰራ ከተከለከለ *በፍፁም ወይ አልፎአልፎ* የሚለውን ውጤት ይስጡ (ወይ መሀከለኛ ደረጃ የሚለው)፡፡ ህፃን ልጅ ምድጃ ሊያበራ ይችላል ነገር ግን ራሱን ችሎ ይሰራል ማለት ግን አይደለም፡፡

**ክትትል**

አመልካቹ የሚደረግለት ክትትል ከሚያስፈልጋት በታች ወይ በላይ ሊሆን ይችላል ይህም እቤት ውስጥ ወይ ድርጅት ውስጥ ባለው የክትትል መጠን መሰረት ያደርጋል፡፡ ቢሆንም የአመልካች ባህሪ መለካት ያለበት ነገሮችን ራሳቸውን ችለው መስራት አቅማቸውን መሰረት በማድረግ እንጂ በአንድ ተቋም ውስጥ ባለው የክትትል ወይ አጠቃላይ ሕግ መሰረት በማድረግ አይደለም፡፡

**ፍቃድ መጠየቅ**

አመልካቹ ስራውን ከመጀመሩ በፊት በተገቢ መልኩ በመጠየቁ ቅጣት አይቀጣም፡፡ ምንም እንኳን አመልካቹ ስራውን ሙሉ በሙሉ ራሱ ባይጀምርም ስራውን ከመጀመሩ በፊት በተገቢ መልኩ በመጠየቅ እየጀመረው ነው፡፡

**ግንዛቤ፣ መነሳሳትና ማሕበራዊ ግዴታ**

*ሳይጠየቅ ጥሩ ይሰራል* የሚለውን ውጤት ለማግኘት አመልካች በአካባቢ ያለውን ማሕበራዊ ግዴታ ግምት ውስጥ በማስገባት ስራውን የመስራት አቅም፣ ስራውን መቼ መስራት እንዳለበት ግንዘቤና የመስራት ተነሳሽነት ያስፈልገዋል፡፡ *መኝታ ቤት ማፅዳት* የሚለው ጥሩ ምሳሌ ይሆናል፡፡

> አልጋ ማንጠፍ **የማይችል** ህፃን ወይ የእጅ አካል ጉዳት ያለበት አዋቂ ካለ ያለው ግንዛቤ ወይ መነሳሳት ምንም ቢሆንም *በፍፁም ወይ አልፎልፉ* የሚል ውጤት ይሰጠዋል፡፡
>
> ስልጠናዎች ካገኘ በኋላ በሚገባ የማፅዳት አቅም ያለውና፣ ነገር ግን ራሱን ችሎ ፕሮግራም መከተል የማይችልና ክህሎቱ አስፈላጊ በሚሆንበት ወቅት **አያውቅም** (ሁሉ ግዜ መጠየቅ አለባቸው)፣ *ሳይጠየቅ ጥሩ ይሰራል* ከሚለው በታች ውጤት ይሰጠዋል፡፡
>
> *ራሱን የቻለ አዋቂና ንፅህናውን በሚገባ የሚጠብቅ ሳይጠየቅ ሰራውን ሳይጠየቅ የሚሰራ፡፡*
>
> *ራሱን የቻላ አዋቂ ሆኖ ሳለ መኝታ ቤቱ ብዙ ግዜ ያማያስተካክል፣ የቅርብ ጓደኞቹ እንኳን ቢመጡ፣ ነገር ግን ለጤና ጎጂ ከመሆኑ በፊት ወይ ሰው ከመምጣቱ በፊት ይፀዳል፣ ጥሩ ይሰራሕ* የሚል ውጤት ሊሰጠው የሚያስችለው እጅ አካል ጉዳት የሌለበት ሰው በተለመደው የአኗኗር ዘዴ በተለመደው **ማሕበራዊ ኑሮ ላይ በሚጠበቀው** *መጠን በተደጋጋሚ* የሚያፀዳ ከሆነ ነው፡፡
>
> ቤቱን በሚገባ የማፅዳት አቅም ያለው የቤተሰቡ አባል፣ ዝቅተኛ የሆነ ንፅህና አጠባበቅ ያለው ማነው፣ ነገር ግን የቤቱ ሕግ በሚያስቀምጠው፣ መመርያ መሰረት ‹‹ሰው ሲኖር›› በደንብ የሚያፀዳው ማነው፣ *ጥሩ ይሰራሕ* የሚል ውጤት ሊሰጠው የሚያስችለው አንዳንድ ከሚሰጡ አስተያየቶች ወይ ማስታወሻዎች ውጪ **በቤት ውስጥ የሚጠበቅበትን** የሚተገብር ከሆነ ነው፡፡
>
> በሚገባ የማፅዳት አቅም ያለውና ነገር ግን ራሱን ችሎ ፕሮግራም መከተል የማይችልና ማሕበራዊ መስተጋብሩ እንዲያደርግ በግልፅ የሚያስቀምጠውን ክህሎቶችን መተግበር የማችል የማይገነዘብ ወይ **ተነሳሽነት** የሌለው፣ ምናልባትም ከአእምሮ ጤና ችግር ጋር የሚያያዝ ከሆነ *ሳይጠየቅ በሚገባ የሚተገበር* ከሚለው በታች ያለውን ውጤት ሊሰጠው ይገባል፡፡

**ጥያቄ ዎች?**

## ICAP መሙላት የሚችለው ማነው?

ግምገማ ከሚደረግበት ሰው ጋር በሚገባ የሚተዋወቅ ማንኛውም ወላጅ፣ አስተማሪ ወይ ተንከባካቢ ሰው ICAP ለመሙላት የሚያስፈልገውን መረጃ መስጠት ይችላል፡፡ በመመርያው መሰረት ምላሽ ሰጪው ቢያንስ ለሶስት ወራት በየቀኑ ይገናኙ ከነበረ እሱ/እሷ አመልካቹን በሚገባ ማወቅና ICAP ባህሪውን አመልካቹን በሚያውቀው መጠን ያህል መሙላት እንዳለበት/ባት ያስቀምጣል፡፡ ምላሽ ሰጪው ICAP ቡክሌት በቀጥታ መሙላት (ለመሙላት ICAP መመርያና ICAP አባሪ D መሰረታዊ መመርያ የሚያውቁ ከሆነ) ወይ እንደ ማሕበራዊ ሰራተኛ የመሳሰሉ ጠያቂዎችን መረጃ መስጠት ይችላል፡፡ ስለ ሰውየውና ባህሪው የተሰጠው መረጃ ግዜውን የጠበቀና ትክክል እስከሆነ ድረስ መረጃው ከየትና እንዴት ተገኘ የሚለው አስፈላጊ አይደለም፡፡ የተያዩ ምላሽ ሰጪዎች ሊጠየቁ ይችላሉ፡፡

### ምላሽ ሰጪው ከልክ ያለፈ ጥበቃ ወይ እያታለለ እንደሆነ ካወቅኩኝስ ወይ ሁለት ምላሽ ሰጪዎች ካልተስማሙስ?

በጣም ከልክ ያለፈ ጥበቃ የሚያደርግ ወላጅ ‹‹ይህን ማድረግ ይችላል ግን እንዲያደርግ አልፈቅድም›› ሊል ይችላል፡፡ የሚያታልል ምላሽ ሰጪ ደግሞ ‹‹ማድረግ ይችላል ነገር ግን አያደርገውም…›› በማንኛውም ሁኔታ ዓላማው አሁናዊና ትክክለኛ የሆነውን መረጃ ለማግኘት መያዝ ነው፡፡ አመልካቹ ክህሎቱን በተገቢ መልኩ እንደቻለውና ዕድል ከተሰጣቸውን ደህንነቱ በተጠበቀ መለኩ ስራውን መስራት እንደሚችሉ ለመለየት ተጨማሪ ጥያቄዎች ይጠየቃሉ፡፡ አስፈላጊ ከሆነ የሰበሰብከው መረጃ አመልካቹ በማንኛውም ሁኔታ ያለውን ትክክለኛ ባህሪ የሚያሳይ አጥጋቢ መረጃ እስኪታገኝ ተጨማሪ መላሾችን (ወላጅ፣ አስተማሪ፣ ስራ ባልደረባ ወይ እራሱ አመልካቹንም) ማነጋገር፡፡

### ክፍት ቦታ የተተወ ጥያቄ ካለስ?

ጥያቄ ሳይመለስ ከተተወ ፈተና ውጤት ሊሰጠው አይችልም፡፡ ለእያንዳዱ ጥያቄ ላይ ካሉት አራት ዶሜኖች አንድ መልስ ላይ ምልክት ያድርጉ (77 አይተሞ)፡፡

### ሰውየው አንዳንድ ነገሮች ላይ ያለውን አቅም ካላወቅኩስ?

አመልካቹ ይህን እንቅስቃሴ ሲተገብር ካልተመለከቱ ወይ አመለካቹ ይህን ለማድረግ እድል ካላገኙ ወይ እንዲተገብሩ ሀላፊነት ካልተሰጣቸው ይህን የተመለከተ ሰው ካለ ይጠይቁ ወይ አመልካቹ ድጋፍ ሳያገኝ ወይ ተጨማሪ ስለጠና ሳያገኝ ምን ያህል ማድረግ ይችላል የሚለውን ይገምቱ፡፡ ግምቶትም ያሰው ተመሳሳይ ወይ ተዛማጅ እንቅስቃሴዎችን ሲያደርግ ባደረጉት ክትትል ወይ መረጃ መሰረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡

### እዚህ ባህሪ ላይ ጊዝያዊ ህመም ወይ ጉዳት ጫና ካሳደረስ?

በአጠቃላይ ባለፉት ጥቂት ወራት ውስጥ አመልካቹ ያለውን አማካኝ እቅስቃሴ ውጤት መስጠት፡፡ ተቀባይነት እንዲኖረው፣ ፈተናው በአንድ ግዜ ተለዋዋጭ ባህሪ መለካት አለበት፡፡ የሚቻል ከሆነ ይህ በእርግጥም የታመመው ሰው እስኪረጋጋ የግምገማ ሂደቱን ማዘግየት፡፡

### የአእምሮ ጤና ችግር ያላቸውስ፣ አፈፃፀማቸውም በሂደት ወይ ከጊዜ ወደ ጊዜ ሊቀየር ስለሚችል?

በአጠቃላይ ባለፉት ጥቂት ወራት ውስጥ አመልካቹ ያለውን አማካኝ እቅስቃሴ ውጤት መስጠት፡፡ ተቀባይነት እንዲኖረው፣ ፈተናው በአንድ ግዜ ተለዋዋጭ ባህሪ መለካት አለበት፡፡ የሚቻል ከሆነ ይህ በእርግጥም የታመመው ሰው እስኪረጋጋ የግምገማ ሂደቱን ማዘግየት፡፡

ያለፈው ወር የታየው ባህሪ ዓመቱን በሙሉ የነበረው የሚያመላክት ከሆነ፣ አሁን ያለው የአእምሮ ጤና ችግርም (ወይ የሌለው) ተመሳሳይ ሊሆን ስለሚችል ይህን ባህሪ ለማመሳሰል ዓመት ሙሉ ተመሳሳይ ክትትል ሊያስፈልግ ይችላል፡፡ ድጋሚ *ይህ የፖሊሲ ጥያቄ እንጂ የግምገማ ጥያቄ አይደለም* ፖሊሲ እያንዳንዱን ስቴት ወይ ኤጀንሲ የሚገልፅ ሲሆን፣ እንዲሁም ዓመት ሙሉ የሚካሄድ ጉዳይ አስተዳደር ሂደት ላይ ‹‹የከፋ ሁኔታ›› እና ‹‹ጥሩ ሁኔታ›› ICAP ሊኖር ይችላል፡፡

**ፔዶፊል ወይ አርሶኒስት ወይ ሌላ የመልመድ ባህሪው ከፍተኛ የሆነና ራሱን ችሉ የመስራት አቅሙም በሚያስፈልገው ተከታታይ ክትትል የተገደበ ከሆነስ?**

የአመልካቹ የመልመድ ባህሪ ውጤት ሊሰጠው የሚገባው ያንን ስራ ራሱን ችሎ ማድረግ ሲችል ነው እንጂ በባህሪ ችግሩ ምክንያት መደረግ የነበረበትን የክትትል ደረጃ ላይ መሰረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡ አመልካቹ አንድ ስራ ማለትም *ከጓደኞቹ ጋር ውጪ ሲሆን ተገቢውን ባህሪ ለማሳየት የሚጥር* ከሆነ (ወይ ማድረግ ከቻለ)፣ ምንም እንኳን ብቻውን ከጓደኞቹ ጋር መውጣት ባይኖርበትም ለዚህ ስራው ውጤት ማግኘት አለበት፡፡ ይህ ዓይነት እንቅስቃሴ ከመልመድ ባህሪ ውጪ ተጨማሪ ክትትል ያስፈልገዋል ምክንያቱም ባላቸው መጥፎ ባህሪ ነው፡፡ አንዳንድ ስቴቶች ከ ICAP ውጤት በተጨማሪ ሌሎች ተጨማሪ ጥያቄዎችን ይጠቀማሉ ይህም ለነዚህ ልዩ ሁነቶች የክትትል ደረጃ ለማዘዝ ያስችላል፡፡ በድጋሚ *ይህ የፖሊሲ ጥያቄ እንጂ የግምገማ ጥያቄ አይደለም*፡፡